**ዳግ (DAG) በሚል አህጽሮት የሚጠራው በኢትዮጵያ የእርዳታ ለጋሾች ስብስብ የህዩማን ራይትስ ዎችን ሪፖርት ተንተርሶ በሰጠው መግለጫ ላይ የተሰጠ መግለጫ**

**ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)**

ህዩማን ራይትስ ዎች የተባለ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት በኢትዮጵያ ድሆችን ለመመገብና ለመርዳት ተብሎ በዓለም አቀፍ ማሕበረሰብ የሚለገሰው እርዳታ የተረጂውን ሕዝብ ዴሞክራስያዊና ሰብአዊ መብቶች ለማፈን ዓላማ እየዋለ መሆኑን በማስረጃ በማስደገፍ ወቅታዊ ሪፖርቱን ይፋ አድርጓል። ይህንን ተከትሎም ገዢው ፓርቲ "ኒዮሊበራሎች" እያለ ሲያጣጥላቸው፤ ሲያሰኘው ደግሞ "ብትፈልጉ ወደ ሲማሊሞ ገደል ግቡ" እያለ ሲያሸብራቸው የከረመው የምጽዋት ጌቶች ከገዢው ፓርቲ ጋር በየፊናቸው የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቹ ድርጅት ይፋ ያደረገውን ሪፖርት የሚያጣጥል ቅጽበታዊ የአጸፋ መግለጫዎች አውጠተዋል።

ህዩማን ራይትስ ዎች በጓንታናሞ ቤይና በአቡግሬብ እስር ቤቶች የተፈጸመውን የሰብአዊ መብት ጥሰት፤ የእስረኞችን ሰብአዊ መብት ለመጣስ እንዲመች ተብሎ ረንዲሽን (Rendition) ተብሎ የሚታወቀውን እስረኞችን ከአገር አገር የማዞር ስልትን አጥብቆ በመቃወም የሚታወቅ፤ ሃያል ደካማ፤ ድሃ ሃብታም፤ ሳይል የሰብአዊ መብት ጥሰት የሚፈፀሙትን ሁሉ አምርሮ በመተቸት የሚታወቅና በዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ዘንድ ትልቅ አመኔታ ያተረፈ አለምአቀፍ ድርጅት ነው። በዚህም ምክንያት ይፋ የሚያደርጋቸው ሪፖርቶች በዓለምአቀፍ የመገናኛ ብዙሃን በኩል ሰፊ ሽፋን ይሰጣቸዋል፤ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፤ የአሜሪካ ኮንግረስ፤ የአውሮፓ ፓርላማዎች እንደዚሁም ግብር ከፋዩ የዓለም ማሕበረሰብ ይህ ድርጅት ለሚያወጣቸው ሪፖርቶች ጆሮአቸውን ሰጥተው በትኩረት እንደሚከታተሉትም ይታወቃል።

ዳጎችና የኢትዮጵያው አምባገነን አገዛዝ ህዩማን ራይትስ ዎች በሰማንያ ሚልዮን ኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ ይፋ በመውጣቱ የሰጡት የአጸፋ መልስ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር በሁለቱም መካከል የትኛውም ልዩነት ቢኖር በድሃው ኢትዮጵያዊ የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት ረገጣ ላይ ግን እጅጉን የተቀራረበ አቋም እንዳላቸው ነው። ይህ

ባይሆን ኖሮ ለጋሾቹ ምርጫ 2002 የሆነውን እያወቁ፤ በኢትዮጵያ ያለውን የፖለቲካ ምህዳርና አፈና እያወቁ እንዲሁ ተግተልትለው ባልወጡ ነበር።

ለጋሾቹ ለአገዛዙ ይሰጡት የነበረውን ቀጥተኛ የባጀት ድጋፍ አቁመው በምትኩ ፒቢስ (PBS) እና ሴፍቲ ኔት (PSNP) የሚባሉትን ፕሮግራሞች ሲያመጡ ምክንያታቸው አፋኙ አገዛዝ ምርጫ 97ን ተከትሎ በወሰደው ጨካኝ እርምጃ ያስከተለውን ዓለምአቀፍ ውግዘት መሆኑ ይታወቃል። ይህ ለውጥ ተደረገም እርዳታው በአንድ በኩል ለታለመለት ዓላማ እንዲውልና ድሃው እንዲጠቀም በሌላ በኩል ደግሞ የተሰጠው እርዳታ ሕዝብን ለማፈን በመሳርያነት እንዳይውል የሚከላከሉ የተለያዩ የቁጥጥር ዘዴዎች አበጅተናል ሲሉ ቆይተዋል።

አበጅተናል ያሉት የቁጥጥር ዘዴም አልሰራም። ይልቁንስ ኢህአዴግ ይህንን እርዳታ በገጠሪቷ ኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ ፍጹማዊ አገዛዝ ለመፍጠር ተጠቅሞበታል። ተቃዋሚዎች ይህንን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችንም ሲያቀርቡ ቆይተዋል። ምሳሌያዊ ማሳያ ይሆናሉ ተብለው፤ በደረሰባቸው በደል መስክርነታቸውን ለመስጠት አዲስ አበባ ድረስ የመጡ የትግራይ አርሶ አደሮች በነጭ ለባሽ የድህንነት ሃይሎች ታፍነው መሰወራቸው፤ ከዚያም ተገደው ወደመጡበት እንዲመለሱ መደረጋቸው ከዚህ ቀደም ይፋ መደረጉ ይታወሳል። እንዲሁም ቦታው ድረስ ሄዶ እውነታውን ለማጣራት የተንቀሳቀሰው የብሉምበርግ ጋዜጠኛ ጄሰን በደህንነቶች ታስሮ ከመቀሌ አዲስ አበባ እንዲመጣ መደረጉ፤ በሃያ አራት ሰዓት ኢትዮጵያን እንዲለቅ መታዘዙ፤ ኢትዮጵያ ካለው የአሜሪካ ኢምባሲ ጋር በተደረገ ውይይት የጋዜጠኛው መባረር መገታቱም ይታወቃል። ይህን ለምሳሌ ያህል ጠቀስን እንጅ በመላ የሴፍቲኔት ፕሮግራም በተዘረጋባቸው የሀገራችን ክፍሎች የተፈፀመው ከዚህ የተለየ አይደለም።

ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው አፋኝ ሁኔታ ምክንያት መንግስት በደለ ብሎ ምስክርነት ለመስጠት እጅግ አስቸጋሪ መሆኑ የዳጉ ስብስብ ጁላይ 2010 ባወጣው ሪፖርት ተመልክቷል። እንደዚህ ባለ አስፈሪ ሁኔታ ውስጥ ምስክርነታቸውን ለመስጠት የመጡት ዜጎች እና የእነሱን ሁኔታ ለማጣራት የሞከረው ጋዜጠኛ ያጋጣማቸውን ችግርም አሳምሮ ያውቃል። ዳግ አሳምሮ የሚያውቀውን እውነታ ለመናገር ሞራል ማጣቱ ሳይበቃ እርሱ ሊናገረው ይገባ የነበረውን እውነታ ይፋ በማውጣቱ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ተሟጋቹን ድርጅት ለማውገዝ መሽቀዳደሙ ስብስቡን ለትዝብት ዳርጎታል። ይህ ተግባሩ በኢትዮጵያ የተንሰራፋው ጭቆና ጠበቃም አስመስሎታል።

ዳግ ኦክቶበር 22 ባወጣው መግለጫ፣ እርዳታ ለፖለቲካ መሳርያነት እየዋለ ነው የሚለውን ስሞታ ተከትለን ባደረግነው ማጣራት እንደዚህ ያለ ሁኔታ አለመኖሩን አረጋግጠናል የሚል አስተያየት ሰንዝሮአል። በሁለት ምዕራፍ ይከናወናል የተባለው የማጣራት ስራ ሙሉ በሙሉ ሳይጠናቀቅ ጁላይ 2010 ላይ የወጣው የዳግ ሪፖርት ተመልከተነዋል። ማጣራቱ ሳይጠቃለል የመጀመርያውን ምዕራፍ ስራ ሪፖርት ብቻ ለምን በጥድፊያ ለማውጣት መፈለጉ የራሱን መልክት በውል ያስተላልፋል። ሪፖርቱ ደራስያን ራሳቸው ህዩማን ራይትስ ዎች አሁን ይፋ ያደረገው ዘገባ እንደሚያወጣ መጠቆማቸው ለተመለከተ እውነትም የጁላዩ ሪፖርቱ የህዩማን ራይትስ ዎችን ዘገባ ለማርከስ የተወረወረ የሳይቀድመን እንቅደመው ምት (pre-emptive) ይሆን ወይ የሚል ጥያቄ አስነስቶብናል። የማጣራቱ የመጀመርያው ምዕራፍ ስራ በለጋሾችና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል ስምምነት የተደረሰባቸውን የቁጥጥር ዘዴዎች ብቃትና ጥንካሬ በመመዘን የተገደብ የቢሮ ስራ (Desk work) እንደነበረና ተፈጸሙ የተባሉትን ክሶች የመመርመርና የማጣራት ዓላማ እንዳልነበረው በራሱ በሪፖርቱ ተገልጿል። ክሱን ለማጣራት አንድም እርምጃ ባልወሰዱበትና ከቢሮ ያልወጣ ስራ ብቻ መስራታቸውን እያወቀም ነው የዳጉ ስብስብ የዴሞክራሲ የሰብአዊ መብት ተሚጋቹ ተቋሙ ያቀረበውን ሪፖርት ከእውነት የራቀ ነው ብሎ ለአጸፋ መልስ የተጣደፈው።

ለኢትዮጵያ ከሚሰጠው እርዳታ በተያያዘ መነጋገርያ ሆኖ ያለው ፍሬ ነገር የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው። ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት ትልቅ ክብር እንሰጣለን የሚሉት ለጋሽ ሃገራት ቅድምያ ሊሰጡት ይገባ የነበረው ይህን ጥሰት እንዲስተካከል በሚሰጡት እርዳታ አማካኝነት በጎ ተጽእኖአቸውን ማሳረፍ ነበር። ጁላይ የወጣው የዳግ ሪፖርት ዋና ጭንቀት ግን ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት ጥሰት አለ የሚለውን ዋና ፍሬ ነገር ማስተካከል አለመሆኑ ከሪፖርቱ መገንዘብ ይቻላል። የዳጎች ዋና ጭንቀት የሆነው ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት ጥሰት በመፈጸሙ ምክንያት እርዳታው እንዳይቋረጥ በሚል ሽፋን ነገሮችን ተሸቀዳድሞ ማድበስበስ መሆኑ እሙን ነው።

ተቃዋሚዎች በተለይ ደግሞ መድረክ በአንድ በኩል ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና ሰብአዊ መብት እንዲጠበቅ እያታገሉና እየጠየቁ በሌላ በኩል ደግሞ እርዳታ እየሰጡ ሁለቱንም ዓላማዎች ማራመድ እንደሚገባና ማሳካትም እንደሚቻል ለጋሾቹን ለማሳመን ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። ከሕዝብ ሰቆቃ ይልቅ የራሱን ስልጣን የሚያስቀድመው የኢህአዴግ አገዛዝ ግን ሕዝባችንን

ለመመገብ የሚያስችል አቅም እንደሌለው እያወቀም ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት ይከበር የሚሉትን “ብትፈልጉ ሊማሊሞ ገደል ግቡ” ሲላቸው ተደምጧል፡፡ እንዲህም እየተባሉ ከዝምታ አልፈው ህዩማን ራይትስ ዎች ያወጣውን ዘገባ እስከማወገዝ መሄዳቸው በአምባገነኑ አገዛዝና በምጽዋት ጌቶቹ መሃከል ያለው ግንኙነት የሚመራው ሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲን በሚያካክሉ ግዙፍ መርሆዎችን ተንተርሶ ሳይሆን በእከክልኝ ልከክህ መርህ መሆኑን አመልካች ነው፡፡

የታላቁ ሕዝባችን የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት አፈና ከቁብ አለመቆጠሩ በጣም አሳዝኖናል፡፡ እኛም ሆነን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለጋሾች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብትን ከልማት ነጥለው ከአምባገነኖች ጋር የሚያደርጉትን መመዳሞድ ማቆም አይቻለን ይሆናል፡፡ ለእርዳታው የሚሆነውን ገንዘብ የሚያቀርበውን የአገራቸው ግብር ከፋይ ይህንን ማድረግ እንደሚቻለው ግን ይገነዘባሉ፡፡ ዳጎች ህዩማን ራይትስ ዎችን ሪፖርትን ለማጣጣል የተሽቀዳደሙት የአገራቸው ታክስ ከፋይ ሕዝብ ሪፖርቱን አይቶ ይህ ሲሆን ምን ታደርጉ ነበር የሚል ጥያቄ እንደሚያነሳባቸው ስለሚያውቁ ነው፡፡ ምን ያህል ይሳካላቸዋል ጊዜ የሚመልሰው ይሆናል እኛና ሕዝባችን ግን ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት ጥበቃ የምናደርገውን ትግል ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ
ጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም
<u>አዲስ አበባ-</u>